

# ማዲባ! ማንዴላ!

(ለአፍሪካ የመንፈስ አባት ለማንዴላ ቀን)




የተፈጥሮን ሕግ ክዳ ቃለ-እግዚአብሔር አርክሳ፣
የሰውን ልጅ ክቡር ፍጡር ከእንሰሳት አሳንሳ፣
ባስነዋሪ ጸያፍ ልክፍት በጸረ-ሰብ ታብታ፣
በአፓርታይድ ክፉ ደዌ በዘር ቀለም በሽታ፣
ስትታመስ፣ ስትጠበስ፣ ስትሰቃይ.. ስትጠቃ፣
ባለ አለላ. . . ባለ ቀለም ደቡባዊት አፍሪቃ. . .፤

... ከኡምታታ ለምለም መንደር፣ ከአፍሪቃ ጥቁር አፈር፣
የጥቁር ዘር የግፍ ዕንባ፣ የወለደው ማዲባ. . .፣
እልህ ፈታኝ፣ አስጨናቂ.. ሕይወት ሙሉ ትግል ጎራ፣
ባፋና! ባፋና! ከኤ ኤን ሲ ጓዶች ጋራ. . .!
... ለሩብ ዘመን ሮቢን ደሴት፣ ከኋላ በር ቢዘጋበት፣
እስር፣ ግዞት.. ሳይበግረው፣ ፍሬ አፈራ የነጻነት!

የተስፋ ምንጭ ፏፏቴ ለዝንተ-ዓለም የምትፈስ፣
ዘረኝነት ደዌ ፈዋሽ ጸበል ላለም እምትደርስ፣
ባለም ታሪክ መቅረዝ ማማ ሥምህ ደምቆ እሚያበራ፣
ያፍሪካ ልጅ ብሩህ ኮከብ! ግብርህ በምድር የተዘራ፤
ያብሮ መኖር የመቻቻል.. የዕርቀ-ሰላም፣ የእኩልነት፣
የአፍሪካ መንፈስ አባት አርአያ ክብር ኩራት፤
ማዲባ! ማንዴላ! ረጂም ዕድሜ! ምዕተ-ዓመት!!
ይሁንልህ መልካም ሕይወት! ይደልዎ! መልካም ልደት!!

ጌታቸው አበራ
ሐምሌ 2002 ዓ/ም
(ጁላይ 2010)